የረቡዕ ታህሳሥ 27 1997 ዓም( ጃንዋሪ 5 2005)

# የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ

## ሀገር እየጠሉ ባዕዳንን መውደድ

*ማወቅ መውደድን ያስከትላል እንዲሉ፥ እራስን ከማወቅ አንስቶ፥ ቤተሰብን፥ ትዳርን፥ ባልንጀራን፥ ሀገርን፥ ወገንን፥ ታሪክን፥ ዕምነትን ባህልን ወዘተ.. በሚገባ ማወቅ፥ መሠረታወዊና ዘለቄታ ጥቅም ይኖረዋል። ማነኛውንም ጉዳይ ውስጡን በሚገባ ማወቅ ማለት፥ ይህንን ያወቁትን ጉዳይ መውደድን ሊያስከትል ይችላል። ማፍቀር ደግሞ ለሰብዓዊ ፍጡር ሁሉ የተሰጠው ፀጋ ነው። በመሆኑም፥ ማወቅና ማፍቀር ተደጋጋፊ በመሆናቸው፥ በማወቅ ላይ የተመሠረተ ፍቅር፥ ዘላቂ እንጅ ለወረትና ለጊዚያዊ ጥቅም የሚበገር አይሆንም። ጀግኖች እራሳቸውን የሚሰዉት ለሀገር ለወገን ካላቸው ፍቅርና ከበሬታ ነው። የኢትዮጵያ ሰማዕታት በዘመናት ደማቸውን እያፈሰሱ ሀገራችንን ሊያቆዩልን የቻሉት፥ ለሀገር ለወገን ፍቅር ሲሉ ነበር። እንዲያውም የአርበኝነት ትክክለኛ ትርጉሙ፥ ሀገር መውደድ ማለት ነው። ስለ ፍቅር፥ በዘመናት ታላላቅ ሃይማኖቶች፤ ፈላስፎች፥ ጠቢባን ደራሲያንና መምህራን ጽፈዋል፥ ሰብከዋል፥ አስተምረዋል፥ ስለፍቅርም እራሳቸውን ሰውተወል ። ይህንን ሁሉ ሊያርጉ የበቁትም፥ የተሰውበትን ጉዳይ በሚገባ ከማወቃቸው የተነሳ ነበር።*

*በዘመናት ኢትዮጵያ ሀገራቸውን፥ ሕዝባቸውን፥ወገናቸውን፥ ባህላቸውን፥ ሃይማኖታቸውን፥ ታሪካቸውን ቅርሳቸውን በሚገባ ያወቁ ሰዎች፥ ዕውቀታቸውን ወደፍቅር በመለወጥ፥ ዕውነተኛ ፍቅር ማለት ምን ማለት እንደሆነ በሚገባ ገልጸው በአኩሪ ታሪካቸው ምዕራፍ አስመዝግበው አልፈዋል። እነኝህ ሁሉ ሰማዕታት ስለሀገራቸው የነበራቸውን ፍቅር የህይወት ዋጋ የከፈሉት፥ ለሹመት ለማዕረግ፥ ለአጉል ዝናና፥ ለከንቱ ውዳሴ፥ወይም ለአላፊ ጠፊ ንብረትና ሀብት አልነበረም። ሀገራቸውን በሚገባ ከማወቅ የተነሳ ከተጎናፀፉት ጽኑ ፍቅር ብቻ ነበር። ውለታ ይከፈለናል፥ከሚልም የቆሳቁስ ጥቅማ ጥቅምም ተነስተው አልነበረም/አይደለም።*

*ሀገራችን በአያሌ ዘመን ህልውናዋ ውስጥ፥ ማንነቷን በሚገባ አውቀው ያፈቀሯት አያሌ ዜጎች ነበሯት፥ ለእርሷ የነበራቸውንም ዕወቀትና ፍቅር ከማንም ከምንም በላይ ቦታ ሰጥተውት አልፈዋል። ሰማዕቱ አቡነ ጴጥሮስ፥ ግንባር ቀደሙን ቦታ ከያዙት ኢትዮጵያውያን መካከል እንደ ምሳሌ የሚቆጠሩ የሃይማኖት አባት ነበሩ። በዱር በገደል ወድቀው የቀሩትና አስታዋሽ ያላገኙት ሰማዕታት ቁጥራቸውን በትክክል ለማወቅ እችላለሁ የሚል ሰው የሚገኝ መኖሩንም እንጠራጠራለን። ከሀገራቸው ውጭ ተሰድደው ለህዝባቸው ፍቅር፥ ለታሪካቸው ክብር፥ለሀገራቸው ኩራት ተአምር ከሰሩት መካከል ዘርዓይ ድረስና አብዲሳ አጋ ለአብነት የሚጠቀሱ ናቸው። ለእነዚህ የታሪካችን*

*ቆንጨዎች ሀውልት መሰራቱ ቀርቶ፥ የረባ መጽሀፍ የተጻፈላቸው መሆኑን እንኳ በዕርግጠኝነት መናገር የሚቻል አይመስለንም፡፡ የታሪክ ምፀቱ ግን፥ ከዛሬ ስድሳ ዓመታት በፊት የሙሶሊኒ ወታደሮች የአክሱምን ሀውልት ወደ ሮማ ወስደው በሚያላግጡበት ወቅት፥ ይህን ውርደት አላይም ብሎ ጀግንነት በመፈፀም አኩሪ ታሪክ ባስመዘገበው፥ በዘርዓይ ድረስ ኮቴ ላይ፥ ሀገር ወዳድነቱ ለኢትዮጵያ ያልሆነው መለስ ዜናዊ ሀውልቱን አስመልሼ በሚል ልሞገስበት ማለቱ ነው፡፡ ሁል ጊዜ መቸም የበሬን ምስጋና አህያ ስትወስድ መቆየቷ የታወቀ ነው፡፡*

*ኢትዮጵያ ሀገራችንን ምን ጊዜም ቢሆን፥ በሚገባ የሚያውቋት- የሚወዷት የሃይማኖት አባቶች፥ አርበኞችና ጀግኖች ሴቶቿና ሰማዕታቷ ብቻ አልነበሩም፡፡ በየወቅቱ በፍቅሯ የነደዱ ፥ ደራሲያን፥ ድምፃውያን፥ ሰዓሊያን፥ የስፖርት ሰዎች፥የሙዚቃ ጠበብት፥ በርካታ ነበሩ፡፡ አሁንም አሉ፡፡ የሚያሳዝነው ግን፥ አብዛኞዎቹ፥ የሥርዓቶቹ ሰለባ እየሆነ ማለፋቸው ነው፡፡ ስማቸው ሲገን ዓይናቸው የሚቀላ ገዢዎች የሀገራችንን ቅርሶች ለችግርና ለመከራ ዳርገዋል፡፡ ዛሬ ወያኔ የሎሬት ፀጋዬ ስም እንዲነሳ አይሻም፡፡ ትላንት ከበደ ሚካዔል በታሪክ ሂደት ስህተት የሰሩ ቢሆኑም ሊከበሩ ሲገባቸው ማንም ዞር ብሎ ሳያቋጥራቸው አልፈዋል፡፡*

*በስፖርት ዓለም ከሄድን ደግሞ፥ ይድነቃቸው ተሰማን የመሰለ በመላው ዓለም የታወቀን ሰው፥ ለአለፉት ግማሽ ምዕተ ዓመት የኢትዮጵያን የዕግር ኳስ ጨዋታን ለከፍተኛ ደረጃ ያደረሰ ሀገር ወዳድ፤ አስታዋሽ ማጣቱ ምን ሊባል ይችላል? የሚገርመው ደግሞ፥ ነቢይ በሀገሩ አይከበርም እንደሚባለው፥ ከሀገሩ ይልቅ የይድነቃቸው ተሰማን ማንነት በሚገባ የተረዳው የሞሮኮ ሕዝበና መንግሥት፥ በስሙ በሞሮኮ ታላቅ ከተማ፥ የስፖርት እስቴድየም ማሰራቱ ነው፡፡ ይህ ለአሁኑ የኢትዮጵያ ትውልድ የሚያሳፈረው እንጅ የሚያኮረው አይመስለንም፡፡ ይድነቃቸው ተሰማና ሌሎቹ ዕልፍ አዕላፍ ኢትዮጲያውያን ሰማዕታት ሊከበሩ፥ ሊወደሱና የክብር ቦታ ሊያገኙ የሚገባቸው ነበሩ፡፡ የአበበ ቢቂላና የሌሎችም ታሪክ፥ በሙጃ ውስጥ ተቀብሮ እንደማይቀርም የአያሌ ኢትዮጵያውያን ተስፋና ምኞት ነው፡፡ የሜሪ አርምዴንም አሳዛኝ መጨረሻ አንረሳውም፡፡ በተዋናይነቱና በመድረክ ዕውቀቱ ተወዳዳሪ የማይገኝለትን የወጋየሁ ንጋቱን ሀውልት በግሬደር አፍርሶ የመኪና ማቆሚያ ቦታ ማድረግስ ምን ትርጉም ይሰጠዋል? የወያኔ መሪዎችን የሀገር ጥላቻን፥ የሕዝብ ንቀትን ከመግለፅ በስተቀር?*

*የወያኔ መሪዎች በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያላቸውን ጥላቻና ንቀት ሁሉም የሚያውቀው የተረዳው በመሆኑ፥ ዛሬ ከአስራ ሶስት ዓመታት በኋላ፥ እንደ አዲስ ነገር ቆጥሮ ስለሱ ብዙ የሚጨነቅ በአሁኑ ወቅት የሚኖር ዜጋ ያለ አይመስለንም፡፡ የሀገርን ጥቅም የሕዝብን፥ ታሪክ፥ የጀግኖችን፥ የደራሲያንን፥ የስፖርተኞችን ፥ የሊቃውንቱን፥ የተዋንያኖችን፤ የሰማዕታቱን ገድል ፥ ድንቅ ሥራዎችና ዝናና፥ በክብር ጠብቆ የማቆየቱ ኃላፊነት ምን ጊዜም ቢሆን ለአምባገነኖች የሚሰጥ ሊሆን አይገባም፡፡ ይህ መሠረታዊ ተልዕኮና ኃላፊነት*

የሕዝብ ብቻ ነው ሊሆን የሚገባው፡፡ ጨቋኞችማ ደንታ ሊኖራቸው ከቶ አይችልም፡፡ ለሀገር ለወገን የሚጠቅም ተግባርም ይሰሩ ይሆናል ተብሎም አይጠበቅም፡፡ እንዲያውም ከነርሱ በቀር ስሌላ ሰው ማንነትና ምንነት እንዲታወቅ አይፈልጉም፡፡ ካለነርሱ ጀግና፥ አርበኛ ታሪክ ሰሪና ሀገር ወዳድ ያለ አይመስላቸውም፡፡ ከዚህም አልፈው ተርፈው ከእነርሱ በፊት የነበረውን ታሪክና ባህል ከማጥፋትና ከማዋረድ ወደኋላ አይሉም፡፡ ለምሳሌ የአፄው መንግሥት ከእርሳቸው በፊት ስለነበሩት ነገሥታት ታሪክ እንዲነሳ እንዲወሳ አይፈቀድም ነበር፡፡ እንዲያውም ስለበላይ ዘለቀና ስለመሳሰሉት ጀግኖች ታሪክ በአደባባይ መናገር እንደማይቻል የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው፡፡ ደርግም በበኩሉ፥ የአዲስ ታሪክና ሥርዓት መስራች ነኝ ብሎ ስለተወጠረ፥ ከእርሱ በፊት የነበሩትን፥ ጀግኖች ታሪክና ተግባር እንዲነሳ አይፈቅድም ነበር፡፡ ሌላው ቢቀር የታህሳስ 53ቱን ግምባር ቀደም ለውጥ ፈላጊውችን፥ የነ መንግሥቱ ነዋይ፥ ገርማሜ ነዋይ፥ ወርቅነህ ገበየሁ፥ ጽጌ ዲቡና የገርማሜ ወንደ አፍራሽን ታሪክ እንዲቀበር አድርጓል፡፡ የማይጨው አርበኞችን መትሯል፡፡ ሀገር ወዳዶች አድሃርያን ናቸው ብሎ ጨፍጭፏቸዋል፡፡ ደራሲ በዓሉ ግርማን አጥፍቷል፡፡ እርሱን የተካው መለስ በበኩሉ፥ የተከተለው ፈለግ ይህንኑ ነው፡፡ ምሁራንን፤ ታዋቂ ደራሲያንን ያጠፋ ያሰረ፥ ያሳደደ፥ ደብዛቸውን ያጠፋ ነው፡፡ መለስ ዜናዊ ይህን ማድረጉ ግን በጭራሽ የሚፈረድበት ሊሆን አይችልም፡፡ ምክንያቱም ከጥንቱ ከጧቱ አመጣጡና ፍፃሜው ኢትዮጵያን አጥፍቶ በመቅበር ሥነአዕምሮ የተቃኘ በመሆኑ፥ ኢትዮጵያ የምትባል ሀገር ከመቶ ዓመት በፊት አልነበረችም ከሚል መነሻ የተንረደረ ዘረኛ ቡድን መሪ ስለ ጀግኖቿ፥ ደራሲዎቿ፥ አርበኞቿ፥ ምሁሮቿ፥ አርበኞቿና ሀገር ወዳዶች ደንታ ይኖረዋል ተብሎ ማንም አይጠብቅም ፡፡

የወያኔ መሪዎች የተለየ የሚያደርጋቸው ሀቅ ቢኖር፥ ከራስ ፀጉራቸው እስከ እግር ጥፍራቸው ድረስ፥ በኢትዮጵያና በሕዝቧ ላይ ያላቸው ጥላቻና ንቀት ይህ ነው የማይባል መሆኑ ብቻ ሳይሆን፥ለባዕዳን ሰጋጆችና አምላኬዎች መሆናቸውም ጭምርም ነው፡፡ የግል ኩራትና ወኔም ስለሌላቸው፥ በትግል ላይ በነበሩበት ጊዜ ሁሉ፥ አብዮያዊ ዴሞክራሲ የሚሉትንም መፅሂታቸውን ሁሉ ሳይቀር ሲያካሂድላቸው የነበረ የውጭ ዜጋ ነው፡፡ ኢትዮጵያን ለመከፋፈል በሚያደርጉት ጥረትና ሙግት ሰነድ አቅራቢና ጠበቃ፥ ተከራካሪና መስካሪ ያደረጓቸው የውጭ ዜጎችን ነበር፡፡ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን የማያውቅ ደግሞ ይወዳታል ማለት ዘበት ነው፡፡ ስለ ኢትዮጵያ የሚሟገቱ የሀገር ልጆችና አዋቂዎች የጠፉ ይምስል ስዩም መስፍን ወደ አሜሪካ በቅርቡ የተጓዘው የእንግሊዝ አማካሪዎችን አስከትሎ ነው፡፡ የሀገር አወቂዎች የሌሉ ይመስል ወያኔ ባዕዳንን እያስገባና እየቀጠረ የሀገራችንን ገንዘብ ያባክናል፡፡ የሚያደርገው ግን ኢትዮጵያውያንን ባለማመኑ ነው፡፡ በጥፋት ሴራው ንፁህ ዜጋ አይካፈልልኝም ብሎ ስለሚሰጋና ለባዕዳን አሰጋገዱ ደግሞ ሀገር አዋራጅና አፀያፊ መሆኑን ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ከሀገሬው ባዕዱ ይሻለዋል፡፡ ይህ የወያኔ ፀረ ኢትዮጵያነት ጠባይ ዛሬም ቢሆን ፈፅሞ አልተለወጠም፡፡ ስለዚህም ሀገር ወዳድ ኃይሎችና ወያኔ ሊስማሙ የሚችሉበት ሁኔታ ዛሬም የለም፡፡ ስለዚህ

**ዛሬም ቢሆን የሕዝባዊ ትግሉ ዋና ዓላማና ግብ የወያኔን አገዛዝ ማስወገድ መሆን አለበት፡፡ ለባዕድ ያደረና ሀገራችንን የሚጠላ ቡድን በገዢነት ሊቀጥልብን መፍቀድ-መቻል፤ መሸከም ከቶም የለብንምና ነው፡፡**